# ጥናት ላይ ለሚሳተፉ መረጃ

ብሔራዊ የማህበራዊ ምርምር ማዕከል (NatCen) ሰዎች ስለዩናይትድ ኪንግደም (UK) የኢሚግሬሽን ስርዓት ለውጦች ያላቸውን ግንዛቤ እና እይታ ለመረዳት ምርምር እያካሄደ ይገኛል።

የሚከተሉትን ሰዎች እያነጋገርን ነው፡-

- በጃኑዋሪ 2023 ውስጥ ወይም ከዚያ በኋላ በዩኬ ውስጥ ጥገኝነት ጠይቀው ከሆነ እና/ወይም
- በጃኑዋሪ 2023 ውስጥ ወይም ከዚያ በኋላ የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ ሊሆኑ ይችላሉ ተለብለው ወደ ብሔራዊ የሪፈራል ዘዴ (National Referral Mechanism) ተልከው ከሆነ

ይህ ጥናት ድጎማ የሚደረግለት **በሆም ኦፊስ ነው**፣ ነገር ግን NatCen **ራሱን የቻለ** ድርጅት ነው። ይህም ማለት የሆም ኦፊስ ወይም የመንግሥት አባል አይደለንም፣ እናም **ሰዎች በዩኬ መቆየት ይችሉ እንደሆነና እንዳልሆነ አንወስንም።**

## ምን ማድረግ ይጠበቅብኛል?

እዚህ ሥራ ላይ ለመካፈል፣ የጥናት ቃለ መጠይቅ ማድረግን ያጠቃልላል።

- ቃለ ምልልሱ ከ **NatCen ተመራማሪ** ጋር ይሆናል እናም ከ60-90 ደቂቃዎች ይፈጃል።
- ቃለ መጠይቁን **ከእንግሊዘኛ ውጪ በሌላ ቋንቋ** ማድረግ ይችላሉ። አስተርጓሚ መጠቀም እንችላለን።
- የሚፈልጉ ከሆነ የሚደግፍዎ ሰው ሊኖርዎ ይችላል።
- ቃለ መጠይቁን ለእርስዎ በሚስማማ ሰዓት **በስልክ፣ በቪዲዮ ወይም በአካል** ለማድረግ መምረጥ ይችላሉ።
- በዚህ ሐሳብ **ከተስማሙ ቃለ መጠይቁ** ላይ የሚነግሩንን ምንም ነገር እንዳይረሳ **እንቀዳዋለን።**
- ለጊዜዎ ለማመስገን **£40 ቫውቸር** (**መገበያያ**) ይሰጥዎታል።
- ስለ ተሞክሮዎ ይበልጥ ለማወቅ ተጨማሪ ጥናት ላይ እንዲካፈሉ ልንጠይቆዎት እንችላለን።

## ስለ ምንድን ነው የሚጠይቁኝ?

ቃለ-መጠይቁ ከመጀመሩ በፊት ጥያቄዎቻችን ለእርስዎ ተስማሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለ እርስዎ አንዳንድ ጥያቄዎችን እንጠይቅዎታለን፣ መቼ እንደመጡ እና ስለ ኢሚግሬሽን ማመልከቻዎ።

በቃለ መጠይቁ ወቅት የሚከተሉትን ነገሮች ልንጠይቅዎ እንችላለን፡-

- ስለተለያዩ የጥገኝነት ጥያቄ ስርዓት ክፍሎች ያለዎትን ግንዛቤ
- አግባብነት ባለው ቦታ ከጥገኝነት ጥያቄ ስርዓቱ ጋር የነበረዎትን ተሞክሮ
- በቅርብ ጊዜ በተደረጉ ወይም በታቀዱ የጥገኝነት ህጎች እና ሂደቶች ለውጦች ላይ ያለዎትን እይታ

- እነዚህ ለውጦች በእርስዎ ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ባሉ ሌሎች ሰዎች ላይ እንዴት ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ

በአገርዎ ምን እንደደረሰብዎት ጥያቄ አንጠይቅዎትም።

የምርምር ቃለ መጠይቅ የኢሚግሬሽን ቃለ መጠይቅ አይደለም – ከጥገኝነት ማመልከቻው ጋር አይገናኝም። **ሰዎች በዩኬ መቆየት ይችሉ እንደሆነ አንወስንም ወይም በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይ የሰጡትን መረጃ ይህን ውሳኔ ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር አንጋራም**።

የማትፈልጉትን ማንኛውንም ጥያቄ ላለመመለስ ሊመርጡ ይችላሉ።

## መሳተፍ ግዴታዬ ነው?

ካልፈለጉ በዚህ ጥናት ላይ **መሳተፍ የለብዎትም**። መሳተፍ ወይም አለመሳተፍ **በኢሚግሬሽን ጉዳይዎ** ወይም አሁንም ሆነ ወደፊት እዚህ የመቆየት መብትዎ ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አያሳድርም።

የማትፈልጉትን **ማንኛውንም ጥያቄ ላለመመለስ መምረጥ ይችላሉ** እናም ምንም ምክንያት ሳትሰጡ ከቃለ መጠይቁ በኋላ እስከ 6 ሳምንት ድረስ **መረጃዎቻችሁ ከጥናቱ መዝገብ እንዲወገዱ መጠየቅ ይችላሉ**።

## የምሰጥዎ መረጃ ምን ይደረጋል?

የሚሰጡት መረጃ በሙሉ፣ በመረጃ አያያዝ ሕግ መሰረት በጥብቅና አስተማማኝ ሁኔታ ይቀመጣል እንዲሁም በፕሮጀክቱ መጨረሻ ላይ ይደመሰሳል። እርስዎም ሆነ ሌሎች እንደ እርስዎ ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ያሉ ሰዎች ስላጋጠማችሁ ዋና ዋና ጉዳዮች ለሆም ኦፊስ ሪፖርት እንጽፋለን። ሆም ኦፊስን ጨምሮ በጥናቱ ላይ ማን እንደተሳተፈ ወይም ምን እንዳሉ **ለማንም አንናገርም**። በሪፖርቱ **ውስጥ የማንንም ስም፣ የጉዳዩን ቁጥር ወይም ዝርዝር ጉዳይ አንጨምርም**።

የእርስዎን መረጃ እንዴት እንደምንጠቀም እና እንደምናስቀምጥ ተጨማሪ መረጃ እዚህ ላይ ይመልከቱ - www.natcen.ac.uk/migrantexperiences/privacynotice

## ለጉዳዬ ድጋፍ ማግኘት የምችለው ከየት ነው?

የሚከተሉት ድርጅቶች ስለ ኢሚግሬሽን አሰራር ድጋፍ ወይም መረጃ ሊሰጡዎት ይችላሉ።

### Migrant Help
**ድረገጽ**: www.migranthelpuk.org
**የእርዳታ መስመር** (የነጻ ስልክ በቀን 24 ሰዓታት): 0808 8010 503
**ኢሜል**: ማይግራንት ሄልፕን በሚከተለው መንገድ ያኙዩዋቸው webchat ወይም online enquiry form.

### Refugee Council
**ድረገጽ**: www.refugeecouncil.org.uk
**የእርዳታ መስመር** (9:30 ጠዋት -12:30 ከሰዓት ሰኞ – ሓሙስ): 0808 196 7272

**ኢሜል**: [refugeeadvice@refugeecouncil.org.uk](mailto:refugeeadvice@refugeecouncil.org.uk)

**Samaritans**
**ድረገጽ**: [www.samaritans.org](http://www.samaritans.org)
**የእርዳታ መስመር** (የነጻ ስልክ በቀን 24 ሰዓታት): 116 123

**ኢሜል**: [jo@samaritans.org](mailto:jo@samaritans.org)

## ከእኛ ጋር ይገናኙ

**ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ወይም የቃለ መጠይቁን ጊዜ መቀየር ከፈለጉ** እባክዎ ያነጋግሩን።

- [migrantresearch@natcen.ac.uk](mailto:migrantresearch@natcen.ac.uk)
- 0808 168 2791
- www.natcen.ac.uk/migrantexperiences

*በዚህ ጥናት ውስጥ የተወሰኑ ቦታዎች ብቻ ናቸው ያሉት። ይህ ማለት **መሳተፍ እንደሚፈልጉ የሚነግሩንን ሁሉ ቃለ መጠይቅ ማድረግ ላንችል እንችላለን ማለት ነው።***